## <u>አባሪ</u>

### <u>በአንቀፅ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት</u>
### <u>ሚኒስቴሩ የንግድ ሥራ ፈቃድ</u>
### <u>የሚሰጥባቸው የንግድ ሥራዎች</u>

1/ ላኪነት

2/ አስመጪነት

3/ ላኪነትና አስመጪነት

4/ የውጭ ንግድ ረዳትነት

5/ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም

6/ ሆስፒታል

7/ ክልል ዘለል ሆቴል

8/ ክልል ዘለል የቱሪስት አገልግሎት

- ሳፋሪ
- ማስጎብኘት
- ሳፋሪ ማስጎብኘትና የጉዞ ወኪል

9/ አገር አቋራጭ የመንገድ ማመላለሻ አገልግሎት

- የሕዝብ ማመላለሻ
- የጭነት ማመላለሻ

10/ ሥርጭታቸው በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የተወሰነ ከሆኑት ጋዜጦችና መጽሔቶች በስተቀር ማናቸውም የፕሬስ ሥራዎች

11/ የጉምሩክ አስተላላፊነት

12/ የፈጣን ፖስታ አገልግሎት

13/ የውጭና ገቢ ንግድ እቃዎች ኢንስፔክሽን አገልግሎት

14/ በውጭ ባለሀብት የሚቋቋም የግብርና ልማት

15/ በውጭ ባለሀብት የሚቋቋም ኢንዱስትሪ

16/ በውጭ ባለሀብት የሚቋቋም ማንኛውም የአገልግሎት ሥራ

- ግብርና አገልግሎት
- የኢንጂነሪንግ ወይም ሌላ የቴክኒክ ምክር አገልግሎት
- ደረጃ አንድ ሥራ ተቋራጭነት ወይም የኮንስትራክሽን አማካሪነት
- የውሃ ነክ አገልግሎት ሥራዎች፤
- የጤና ነክ አገልግሎት ሥራዎች፤
- የባለኮከብ ደረጃ ሆቴሎች፤
- አለም አቀፍ ደረጃ ያላቸውና በተወሰነ አገር ምግብ አዘገጃጀት የሚታወቁ ምግብ ቤቶች

17/ - በሕግ ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀዱ ሌሎች የንግድ ሥራዎች

18/ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ባይካተቱም ሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይገባል ብሎ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወስናቸው ሌሎች የንግድ ሥራዎች።